# የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት ብድር
# <u>አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 233/2013</u>

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መመሪያ ቁጥር 29/2008 አንቀጽ 22 የምክር ቤቱ አባላት በተመረጡበት የስራ ዘመን ለመቋቋሚያ የሚውል የ2(ሁለት) ወር ደመወዝ ሊበደሩ እንደሚችሉ የተደነገገ በመሆኑ፣

በዚህ መመሪያ መሠረት ብድር የሚሰጥበትና ብድሩ ተመላሽ የሚደረግበትን ሁኔታ የሚወስን መመሪያ ማውጣት በማስፈለጉ፣

ከዚህ የሚከተለው መመሪያ ወጥቷል፡፡

## 1. አውጭው ባለሥልጣን

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 አንቀጽ 75(1)በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## 2. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ “ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት ብድር አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 233/2013” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 3. የመመሪያው ተፈፃሚነት

ይህ መመሪያ ተፈፃሚ የሚሆነው በየምርጫ ዘመኑ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባልነት ተመርጠው ለመጀመሪያ ጊዜ የምክር ቤቱ አባል ለሚሆኑ ለሚሰጥ የመቋቋሚያ ብድር ብቻ ይሆናል፡፡

## 4. የመመሪያው ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዓላማ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባልነት ተመርጠው ምክር ቤቱን የተቀላቀሉ አባላት በምክር ቤቱ የመጀመሪያው የስራ ዘመን ወስጥ ሊያጋጥማቸው የሚችለውን የኑሮ መቋቋም ችግር ለመወጣት እንዲችሉ ብድር የሚሰጥበትንና ብድሩ ተመላሽ የሚደረግበትን ሥርዓት ማዘርጋት ነው፡፡

## 5. የብድር ማጠንና አጠያየቅ

5.1 በየምርጫው ዘመን የተመረጠ አዲስ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል ምክር ቤቱ ስራ እንደጀመረ በሚቆጠር 12 ወራት ወስጥ የኑሮ መቋቋሚያ ብድር እንዲሰጠው ፍላጎቱን ለምክር ቤቱ ጽ/ቤት ያቀርባል፡፡

5.2 የምክር ቤቱ ጽ/ቤት ብድር ፈላጊዎችን በመመዝገብ የሚፈለገውን ጠቅላላ የብድር ገንዘብ መጠን የሚገልፅ ጥያቄ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በጽሁፍ ያቀርባል፡፡

5.3 የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር የቀረበለትን ጥያቄ ከገማመ በኋላ ለምክር ቤቱ አባላት የሚሰጠውን ገንዘብ ለምክር ቤቱ ጽ/ቤት ያስተላልፋል፡፡

5.4 ለእያንዳንዱ የምክር ቤት አባል በብድር የሚሰጠው ገንዘብ ከአባሉ የ2(ሁለት) ወር ያልተጣራ ደመወዝ አይበልጥም፡፡

5.5 የምክር ቤቱ ጽ/ቤት ለምክር ቤት አባላት በብድር የሚሰጠውን ገንዘብ ከመስጠቱ በፊት ተበዳሪው ከዚህ መመሪያ ጋር የተያያዘውን የዋስትና ሰነድ ማስፈረም አለበት፡፡

5.6 የምክር ቤቱ ጽ/ቤት ከተበዳሪ የምክር ቤት አባላት በየወሩ የሚሰበሰበውን የብድር ገንዘብ በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ማዕከላዊ ግምጃ ቤት ገቢ ማድረግና በዓመት አንድ ጊዜ እስከ ሰኔ 30 ባለው ጊዜ ከሚኒስቴሩ ጋር የሂሳብ ማስታረቅ ማድረግ አለበት፡፡

## 6. ብድሩ ተከፍሎ የሚያልቅበት ጊዜና የሚከፈልበት የወለድ መጠን

6.1 በዚህ መመሪያ መሠረት ለተወካዮች ምክር ቤት አባል የሚሰጥ የደመወዝ ብድር በ24 ወራት የሚከፈል ይሆናል፡፡

6.2 በብድሩ ላይ 4% ወለድ የሚታሰብ ሲሆን ወለዱ ለተበዳሪው ከሚሰጠው ገንዘብ ላይ በቅድሚያ ተቀናሽ ይደረጋል፡፡

## 7. ስለዋስትና አቀራረብ

7.1 ብድር የሚወስድ የምክር ቤት አባል የሚወስደውን ብድር በማናቸውም ምክንያት ሳይከፍል ቢቀር በብድር ወሉ መሠረት በርሱ እግር ተተክተው ብድሩን የሚከፍሉ ደመወዛቸው ከተበዳሪው የወር ደመወዝ በሁለት ደረጃ የማያንስ፣ እኩል ወይም ከተበዳሪው የወር ደመወዝ በላይ የሆነ ሁለት ዋሶች ማቅረብ አለበት፡፡

7.2 ብድር የሚወስደው የምክር ቤት አባል ባለትዳር ከሆነ/ች የትዳር ጓደኛው/ዋ በብድር ወሉ ላይ በጋራ መፈረም አለበት፡፡

7.3 ዋስትና የሚፈርመው ዋስ ያገባ/ች ከሆነ/ች ባለቤቱ/ቷ በዋስትና ሰነድ ላይ መፈረም ይኖርባቸዋል፡፡

## 8. መመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከ መጋቢት 1 ቀን 2008 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ  መጋቢት 15 **ቀን 2008 ዓ.ም**

አብዱልአዚዝ መሐመድ
**የገንዘብና የኢኮኖሚ** ትብብር
**ሚኒስትር**